# የታላቁ መሪ ፖለቲካዊ መሰረት!

**ክፍል ሁለትና የመጨረሻ**

**ከተስፋዬ ለማ 08-27-14**

በአገሪቱ መንግስት በህዝብ ፍላጎትና ምርጫ ብቻ ወደ ስልጣን የሚመጣበት ስርዓት ተፈጥሯል፡፡ በጠቅላይ ሚኒስትር የህይወት ዘመን የታየውም ይኸው ነበር። እስካሁን ድረስ አራት አገራዊ ተካሂደዋል። አገሪቱን በሕመግስት እዲትመራ ለማድረግ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን አካቶ የያዘ ሕገመግስት ተቀርጿል። በአገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1987 ዓ/ም ምርጫ እንዲካሄድ አድርገዋል።

በወቅቱ 57 የፖለቲካ ፓርቲዎች የተሳተፉበት ምርጫ ለአገሪቱ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ የከፈተ ነበር። በህዝብ የተመረጠ መንግስት ለመጀመሪያ ጊዜ ስልጣን የያዘበትና በአገሪቱ አዲስ ምዕራፍ የተከፈተበት ነበር፤ በ1992 ዓ/ም በተካሄደው ምርጫም 49 የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለውድድር የቀረበቡበት ሲሆን ቀጣዮቹ ምርጫዎችም በተመሳሰይ መልክ የተከናወኑ ነበሩ።

የ1997ቱ ብሄራዊ ምርጫ ሕገ መንግስቱን በሕገወጥ መንገድ በመናድ ስልጣን ለመቆናጠጥ ከፍተኛ ጥረት የተደረገበት፤ አንድ ብሄር በሌላው እንዲነሳ፤ አገሪቱ ውስጥ የነበረው ሰላም እንዲደፈርስ፤ የኢትዮጵያ ህዝቦች ከሰላምና ከልማት ጎዳና ወጥተው መቋጫ በሌለው የእርስ በርስ ጦርነት እንዲዘፈቁ ለማድረግ በተወሰኑ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያልተሞከረ ነገር አልነበረም፡፡ በብሄር ብሄርሄረሰቦች መካከል የእርስ በርስ ግጭት የሚያስገባና ደም መፋሰስ የሚያስከትል ነበር።

ያንን ወሳኝ ጊዜ አቶ መለስ እዲያልፍ አድርገዋል። ጠቅላይሚስትሩ በወሰዱት የሰከነ አመራር አገሪቱ የተረጋጋች ሆና እንትትቀጥል አስችሏል፡፡ ህዝቡን የፖለቲካ

ስልጣኑን ማንም በእብሪት ሳይነጥቀው ያስተዳድረኛል ያለውን የፖለቲካ ድርጅት መምረጥ ችሏል።
የመድብለ ፓርቲ ስርዓት በአገራችን መዘዘርጋት ጠቅላይ ሚስትር መለስ ያሰረጹት ትልቅ ድል በመሆኑ ሳሸራርፍ ማስኬድ ለቀሪዎች የሰጡን አደራ ነው። ማኛውም አካል በህዝም ምርጫ ካልሆነ በስተቀር ወደስልጣን የመምጣቱ መንገድ ተዘግቷል።

ሌላው የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች እኩልነት መረጋገጥ ነው።' ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ የብሄር ብሄረሰቦች እኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነት አገሪቱን ከድህነት ለማላቀቅ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ ልዩነታችን ውበታችን በሚል መርህ ሁሉንም ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦችን አቀራርዋል። በአገራችን የሚገኙ ከ80 በላይ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች በገዛ አገራቸው እንደ ሁለተኛ ዜጋ የሚቆጠሩበትና የራሳቸውን ቋንቋና ባህል መጠቀም እንደ ሃጢያት የሚታይበት ዘመን አክትሟልስል።

በአገራችን የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች እኩልነት ተረጋግጧል፡፡ ሁሉም ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ወኪሎቻቸውን ያለምንም ተፅእኖ በነጻነት የሚመረጡበትና የሚወከሉበት ስርአት ተፈጥሯል፡፡ ይህንን ማስቀጠልና ሳይሸራረፍ እንዲተገበር ማድረግም የቀሪዎች ፈንታ ይሆናል።

የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ተግባብተው አንድ ዓላማ ይዘው ድህነት ላይ እንዲዘምቱ ማድረግ የቻሉ ታላቅ መሪ ነበሩ፣ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ። በአገራችን አንዱ ብሄር በሌላው ጫና የሚያሳድርበት ስርዓት ተገርስሶ ሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች በእኩልነት አገራቸውን የሚገነቡበት ስርዓት አበጅተዋል።

ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ራሳቸውን ማስተዳደር ጀምረዋል፡፡ በነጻነት ራሳቸውን የማስተዳደር መብታቸው ተረጋግጧል፡፡ የአካባቢያቸውን ልማት በማፋጠን የልማቱ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቋንቋቸውን መጠቀምና ማሳደግ የሚችሉበት ሁኔታም ተፈጥሯል፡፡

በራሳቸው ቋንቋ ይጠቀማሉ፤ ልጆቻቸው በመጀመሪያ ቋንቋቸው ይማራሉ፡፡ ሙሁራንና ደራሲያንም በቋንቋቸው ይጽፉሉ፡፡ ወግና ባህላቸውን ያስተዋውቃሉ ያሳድጋሉ። ይህ ሁሉ የተገኘው በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥረት ነው። ይህንን አጠናክሮ መቀጠል ደግሞ የመለስ የልማት ሰራዊት ፈንታ ይሆናል።

ዲሞክራሲንና መልካም አስተዳደርን ሙሉበሙሉ ማስፈን ሌላው አቶ መለስ ዜናዊ በህይወት ዘመናቸው እውን ሆኖ ሊያዩት የሚፈልጉት አንዱ ዓቢይ ጉዳይ ነበር። ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በአገሪቱ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ለማስፈን የተጫወቱት ሚና ቀላል አልነበረም።

እንደሚታወቀው ሁሉ ዲምክራሲ በአንድ ሌሊት እውን የሚሆን ነገር አይደለም። ዲሞክራሲ የሚረጋገጠው በሂደትና ቀጣይነት ባለው ዘመቻ ነው። በአገራችን እያበበ የመጣው ዲሞክራሲያዊ ስርዓት በፈጠነ መንገድ መሄድ መቻሉ ማንም የማይክደው ጉዳይ ነው። ይህ የአቶ መለስ ዜናዊ ውጤትነው። እስካሁን የተገነባው ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ጠብቆ የበለጠ እያጎለበቱ መሄድ ደግሞ የአደራ ተቀባዮች ድርሻ ይሆናል።

የታላቁ መሪ አቶ መለስ ሌላው ስኬት ሰላምን የማረጋገጥ ተግባር ነው። የውስጥ ሰላም በአስተማማኝ መልክ መረጋገጡ ብቻ ለዘላቂ ሰላም በቂ ዋስትና እንደማይሆን የተገነዘበው የኢትዮጵያ መንግስት የአህጉሪቱን ሰላም ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት የጎላ ድርሻ ተወጥቷል፡፡

በኢትዮጲያ የነበረውቅ ሁኔታ የከፋ ነበር፡፡ የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተጣሰበት ስርዓት በመዘርጋቱ ድህነትና ኋላቀርነት በአገሪቱ ተንሰራፈተው ነበር፡፡ ከዚህ ረገድ የሰላም አስከባሪ ሰራዊታችን የፈጠረው በጎ ገጽታ አገር ውስጥ በነበረው የተበላሸ አስተዳደርና ስር የሰደደ ድህነት መሸፈኑ የግድ ነበር፡፡ በአገሪቱ ድህነትና ኋላቀርነት እየተስፋፉና እየከፋ ሂዶ የኢትዮጵያ ህዝብ የነበረውን የሃይለስላሴ ስርዓት ለማስወገድና በምትኩ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ለመገንባት ተንቀሳቀሰ፡፡

ስርዓቱን ማስወገድ ቢችልም የተተካው ወታደራዊ መንግስት ግን አምባገነን አገዛዙን አጠናክሮ ቀጠለ፡፡ በአገሪቱ ውጥረት ነገሰ፣ ዜጎች ያለምንም ፍርድ በየመንገዱ መገደል ጀመሩ፣ የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ሰበአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት በገፍ ተጣሰ፡፡ አምባገነናዊ ስርዓት ነግሶ አገሪቱ ለበለጠ ችግር ተዳረገች፡፡ ወታደራዊ አገዛዙ ከሰላማዊ መንገድ ይልቅ ሃይልና ጦርነትን ማራመድ ጀመረ፡፡ የውጭ ግንኙነቱም ሻከረ፣ የውስጥ ሰላምም ደፈረሰ፡፡ በአገሪቱ የእርስ በርስ ጦርነት ተጀመረ፡፡ ከጎረቤት አገራት ጋርም የባለጋራ ስሜት የሚያነግስ ፖሊሲ መከተል ጀመረ፡፡

ከዚህ አንጻር አገሪቱ የውስጥ ሰላም አጣች፡፡ በአፍሪካ ሰላም ለማስከበርም የምትችልበት አቋም ላይ ስላልነበረች ለ30 ዓመታት ያህል የሰላም ማስከበር ተልእኮ አልተሰጣትም፡፡

ይህ ሁኔታ ለአንደየና ለመጨረሻ ጊዜ ተቀየረ፣ 1983 የነጻነት ታጋዮች ሰው በላውን ስርዓት ደምስሰው አገሪቱን ተቆጣጠሩ፡፡ ከፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ መሰረት መለወጥ ጋር ተያይዞም አገሪቱ ለሰላም የሚትሰጠው ትኩረት ተቀየረ፡፡ ድህነትን መቅረፍና ዘላቂ ልማትን ማረጋገጥ ቀዳሚ አጀንዳ ሆነው ተቀረጹ፡፡ ዘላቂ ልማትን እውን የ ሚሆነው ሰላም ሰላምና መረጋጋት ሲኖር መሆኑን በመገንዘብ አገሪቱ ለሰላም የተለየ ትኩረት ሰጥታ ተንቀሳቀሰች፡፡

በአገር ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰላምንና መረጋጋትን በአስተማማኝ መልክ ማረጋገጥ ተቻለ፡፡ ይሁን እንጂ የአንዲት አገር ውስጣዊ ሰላም ብቻውን ዘላዓቂ ልማትን እውን ለማድረግ በቂ አለመሆኑን የተረዳው የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ለቀጠናው፣ ለአህጉሪቱና ለዓለም ሰላም መረጋገጥ የሚጠበቅበትን አስተዋጽኦ ማድረጉን ቀጠለበት፡፡

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት የውሳኔ ቁጥር 40 መሠረት የኢትዮጲያ የሰላም አስከባሪ ሃይል በ1986 ዓ/ም በሩዋንዳ ተሰማርቶ የፀጥታና የደህንነት ሽፋን በመሥጠት ተልእኮውን በአስተማማኝ መንገድ ተወጣ፡፡ በሁለት ዙር በሩዋንዳ የተካሄደው ዘመቻ በሚመለከት ሮሚዮ ዴለር የተባሉ ጄኔራል ምስክርነታቸውን ሲሰጡ "በሩዋንዳ የተሰማራው የኢትዮጲያ የሰላም አሰከባሪ

ሃይል በሁቱዎችም ሆነ በቱትሲዎች ዘንድ ተቀባይነትንና ተወዳጅነት ማግኘት ችሏል፤ ይህንን ተዓማኒነትና ተወዳጅነትን ያገኘው ግን በሚጠቀመው ሃይል አልነበረም፡፡

ሰራዊቱ በጥሩ ስነምግባር መታነጽም የታላቁ መሪ ወሳኝ ሚና ነበራቸው። ሰራዊቱ ለማንኛውም ነገር አይቸኩልም ሁሉንም በትእግስት ይከታተላል፡፡ ጸጥታውን በአስተማማኝ መንገድ በመጠበቅ በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ህዝቡን ያግዛል፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ ተግባር በሌሎች ዘንድ ያልተለመደ ነው፡" ብለዋል፡፡

እንደ ጄነራሉ ምስክርነት የኢትዮጲያ ሰላም አስከባሪ ሰራዊት ሰላምንና ጸጥታን ከማስጠበቅ ጎንለጎን ለህብረተሰቡ የጎላ ፋይዳ ያላቸው ልማቶችን በሚንቀሳቀስበት አካባቢ ይሰራል ብለዋል፡፡ በኮንጎ የአካባቢው ህዝብ ወደ ዛየር የሚተላለፍበት መንገድ እጅግ ጠባብና አስቸጋሪ እንደነበረ ገልጸው የኢትዮጵያ ሰላም አስከባሪ ሰራዊት ለመተላለፊያ አመች የሆነ ደልድይ መስራቱንም ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ገበሬው ማሳ ድረስ በመሄድ እህሉን በማጨድና በመውቃት እንደሚያግዝ ተመልክቻለሁ ብለዋል፡፡ ሠ

ሰራዊቱ በሄደበት አገር ሁሉ ለህዝብ በሚሰጠው ከፍተኛ አክብሮትና ጸረ ሰላም ሃይሎችን በመደምሰስ ረገድ በሚያሳየው ጀግንነት ተወዳጅ ሆኗል ይላሉ ጄኔራሉ፡፡ በመሆኑም የሩዋንዳው ተልእኮ ስኬት አፍሪካውያን ችግራቸውን በራሳቸው መፍታት እንደሚችሉና ከምዕራቡ የሚያስፈልጋቸው የገንዘብና የሎጀስቲክ ድጋፍ ብቻ እንደሆነ ያስመሰከረ ነበር፡፡

በብሩንዲ መንግሥትና በአማጺያን መካከል የተደረሰው የአሩሽያ ተኩስ አቁም ሰምምነት ተግባራዊ ባለመሆኑ የሰላም አስከባሪ ኋይል በቦታው እንዲሰፍር የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በመወሰኑ የኢትዮጵያ ሰላም አስከባሪ ሰራዊት ወደ ቡርንዲ ተሰማራ፡፡

ብሩንዲ በእርስ በርስ ጦርነት በመዳከሟ በሃገሪቱ የሚደረጉት የሰላም ጥረቶች ለመደገፍ ኢትዮጲያ 1000 ሰላም አስከባሪ ሰራዊት የላከች ሲሆን በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የዘመቻውን መጀመር አስመልክተው "ይህ የሰላም አስከባሪ ሃይል ተልዕኮውን እንደሚወጣ እምነታቸው እንደሆነና የአፍሪካ ህብረት በእምነት የሰጠንን ተልዕኮ በአግባቡ እንደሚፈጽም በማረጋገጥ ይህ ለኢትዮጲያ መንግሥትና ህዝብ ኩራት እንደሚሆን እተማመናለሁ" ብለው ነበር፡፡

የኢትዮጵያ ሰላም አስከባሪ ሰራዊትም የተሰጠውን ሃላፊነት በተገቢው መንገድ መወጣት ችሏል፡፡ ኢትዮጵያ የተሳተፈችበት ሌላው ተልእኮ በላይበሪያ ነበር፡፡ ተልእኮው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት በቁጥር 1509 ባስተላለፈው ውሳኔ መሠረት የተኩስ አቁም ስምምነቱን መፈፀሙን መቆጣጠር፣ ትጥቅ ማስፈታትና ሰላምን ማረጋገጥ የሚል ሃላፊነት ነበር የተሰጠው፡፡

ሰላም አስከባሪው ቀጣይነት ያለው ሰላም ለማምጣት ተግቶ በመሥራቱ ከላይቤራውያን የተሰጠው እውቅናና ክብር የላቀ ነበር፡፡ የሰላም አስከባሪው አዛዡ የነበሩት ብርጋዴር ጄነራል ስዩም "ከላይቤሪያውያን ወንድሞችና እህቶቻችን የተለያዩ ድጋፍና ትብብር በማግኘታችን ሁል ጊዜ ሃገራችን ውስጥ እንዳለን ይሰማናል ስለዚህም ተልዕኳችንና ኋላፊነታችንን ለመወጣት በጣም ረድቶናል።" ብለው ነበር፡፡

በላይቤሪያ ተሰማርቶ የነበረው የኢትዮጵያ የሰላም አስከባሪ ሃይል ከ13 ሺ በላይ አማጺያነን ትጥቅ በማስፈታትና ከ21 ሺ 6 መቶ 29 በላይ ስደተኞች ወደ ቀያቸው እንዲመለሱ ማድረግ ችሏል። ከዚህም በተጨማሪ በአገሪቱ ሰላማዊ ምርጫ እንዲካሄድ የበኩሉን አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡

ኢትዮጵያ የውስጥ ሰላሟን በአስተማማኝ መንገድ በማረጋገጥ በአፍሪካ አህጉር ያለውን ሁከትና ብጥብጥ ለማርገብ በሚደረገው ጥረት ያላት የጎላ ተሳትፎ በሶማሊያና በሱዳንም ቀጥላበታለች፡፡ የሶማሊያ ህዝብ ላለፉት 30 ዓመታት በእርስ

በርስ የጎሳ ጦርነቶች ተዘፍቆ በአገሪቱ ሰላምና መረጋጋት ጠፍቶና ሁከትና ሽብር ተንሰራፍቶ የእለት ተለት ኑሮውን ለመምራት የማይችልበት ሁኔታ ተፍጠረ፡፡

ይህንኑ ክፍተት የተገነነዘበው የአልቃይዳ የምስራቅ አፍሪካ ክንፍ የሆነው አልሸባብም አገሪቱን ተቆጣጠረ፡፡ ከዚያም በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት አወጀ፡፡ የኢትዮጵያ ልማትን ለማደናቀፍና አገሪቱ እያስመዘገበችው ያለውን እድገት ለማደናቀፍ ከኤርትራ መንግስት ጋር ግንኙነቱን በማጠናከር እንቅስቃሴ ጀመረ፡፡

በኢትዮጵያ የሰፈነው ሰላም አገሪቱ በልማቱ ረገድ ጥሩ ውጤት እንዳስገኘላት የተገነዘበው የሻዕቢያ መንግስት በኢትዮጵያ ላይ ባካሄደው እብሪተኛ ጦርነት ቅስሙ ተሰብሮ የተመለሰ ቢሆንም በእጅ አዙር የኢትዮጵያን ሰላም ለማደፍረስ የተለያዩ አጀንዳዎችን ነድፎ መንቀሳቀሱን አላቆመም፡፡ ከእነዚህ መካከል አልሸባብን በማሰልጠንና በማስታጠቅ ሶማሊያን እንዲቆጣጠር በማገዝ ወደ ኢትዮጵያ እንዲዘምት ከፍተኛ እገዛ ሲያደርግለት ነበር፡፡ ይህንን ሁኔታ የተገነዘበው የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስትም አንድም ልማታቸውን የሚያደናቅፍ አካሄድን ለመግታት በሌላ በኩል ደግሞ የሶማሊያ ህዝብን ለመታደግ ሲባል የአልሸባብን አከርካሪ በመስበር አገሪቱ የሽግግር መንግስት እንዲታቋቋም ከፍተኛ ድጋፍ አድርገዋል፡፡ የሶማሊያን ሰላም በዘላቂነት ለማረጋገጥም ከሽግግር መንግስቱና ከአፍሪካ ህብረት ሰላም አስከባሪ ቡድን ጋር በመሆን እስካሁን ድረስ አስፈላጊውን ጥረት በማድረግ ላይ ትገኛለች፤ ኢትዮጵያ፡፡

ኢትዮጵያ ድህነትን ለመቅረፍ የሚያስችላትን እቅድ ነድፋ መተግበር ከጀመረችበት ጊዜ አንስቶ በተደረገው ጥረት ዘላቂ ልማትን ማረጋገጥ የሚያስችል መሰረት መገንባት ችላለች፡፡ ዘላቂ ልማትን እውን ለማድረግ የተገነባው መሰረት የመጨረሻው ጫፍ ለማድረስም እስካሁን የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችን በማስፋት ለውጡን ምሉእ ለማድረግ የአምስት አመት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ተነድፎ ትግበራው ከተጀመረ ሁለት ዓመት ሆኖታል፡፡ ይህ የልማት እቅድ እውን የሚሆነው ግን የአገሪቱና የቀጠናው ሰላም በአስተማማኝ መልክ ሲረጋገጥ

በመሆሙ ለሰላም ከፍተኛ ትኩረት ሰጥታ በመንቀሳቀስ ላይ ትገኛለት፤ በዚህ ረገድም ቀላል የማይባል ስኬትን አስመዝግባለች፡፡

ሰላም በመረጋገጡ፣ አገሪቱ ከጥገኝነት የሚያላቅቃት ትክክለኛ አቅጣጫና የእድገት መስመር እየተከተለች በመሆኗ፣ በብዝሃነት የተዋበ አንድነቷ በመጠናከሩ ለጠላቶቿ የእግር እሳት ሆኖባቸዋል፡፡ ኢትዮጵያ በዓለም ዘንድ ስሟ በመልካም እየተነሳ ለሌሎች አገራት ተምሳሌት እየሆነች በመጣች ቁጥር ጠላቶቿ ስልታቸውን እየቀያየሩ የአገሪቱን ገጽታ ጥላሸት ለመቀባት መፍጨርጨራቸው አልቀረም፡፡ ኢትዮጵያ ከጎረቤት አገራት ጋር በሰላምና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ መደጋገፍና ትብብር በማድረግ ሰላማዊ ግንኙነት የመፍጠር አቅጣጫ በመከተል ላይ ያለች አገር ነች፡፡

በቀጠናውም ሆነ በአህጉሪቱ የሚፈጠሩ ግጭቶች በመፍታት ረገድ ያላሳለሰ ጥረት ባማድረግ ላይ ትገኛለች፡፡ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ሰላምና መረጋጋት መፈጠሩ ብቻ ሳይሆን በመላ አፍሪካ ሰላምን እውን ለማድረግ ኢትዮጵያ የላቀ ሚና ያላት አገር ሆናለች፡፡ ከላይ እንደተገለጸው በአፍሪካ የሰላም ማስከበር ሂደትም የላቀ ስፍራ ይዛ ትገኛለች፡፡ አገሪቱ ሰላምን ለማረጋገጥ እያደረገች ያለው ጥረትና እያገኘች ያለው ውጤት በተባበሩት መንግስታት ድርጅትና በአፍሪካ ህብረት ከፍተኛ ተቀባይነት እንዲኖራት አድርጓታል፡፡ በዓለም ህብረተሰብ ዘንድ የነበራት ገጽታም ባለፉት ሁለት ዓሰርት ዓመታት ሙሉ በሙሉ ተቀይሯል፡፡

በአሁኑ ወቅት 6 ሺ 400 አባላትን የያዘ የሰላም አስከባሪ ሰራዊት በሱዳን ዳርፉርና አብዬ፤ በላይቤሪያና በኮትዲቫር አሰማርታለች፡፡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ባለፉት 21 ዓመታት ከ35 ሺ በላይ የሰላም አስከባሪ ሃይል በተለያዩ ግጭቶችና ውጥረት በነገሰባቸው የአፍሪካ አገራት በማሰማራት ተልእኮዋን በሚገባ ተወጥታለች፡፡ በተለያዩ አገራት የተሰማራው የኢትዮጵያ ሰላም አስከባሪ ሃይል በወታደራዊ ዲሲፒሊን ታንጾ የተሰጠውን ሃላፊነት በሚያኮራ መንገድ እየፈጸመ መመለሱንና አሁን በተመሳሳይ መልክ እየፈጸመ እንዳለ መረጃው ይጠቁማል፡፡

ሰላምን ለማስከበር በተሰማራባቸው  የተለያዩ  የአፍሪካ አገራት ባሰየው ከፍ ያለ ብቃትና ዲሲፕሊን በዓለም ዘንድ እውቅና እና አድናቆትን ያተረፈ ሰራዊት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህ አገራችን ኢትዮጵያ ካስመዘገበቻቸው ዓበይት ስኬቶች መካከል አንዱ ነው፡፡  የውስጥ ሰላማን በማረጋገጥ ለአፍሪካ አህጉር የሰላም አምባሳደር መሆን በቅታለች፡፡

ለዚህ ሁሉ መሰረቱ ታላቁ መሪ መሆናቸው ያደባባይ ሚስጢር ነው። እነዚህን የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የሰላምና የዲፕሎማሲ ግንኙነቶችን  አጠናክሮ ማሰቀጠል የግድ ይላል። የኢትዮጵያ ህዝበ የፖለቲካ ስልጣን ባለቤትነት እውን መሆን፤ የመድብለ ፓርቲ ስርዓት መስፈንና የሃሳብና የፕሬስ ነጻነት መረጋገጥ በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዘመን የተረጋገጡ የፖለቲካ ስኬቶች ናቸው። እነዚህን ስኬቶች ዳር ማድረስ ከቻልን  የአቶ መለስ ራዕይ ተሳካ ማለት ነው። እሳቸውም ህያው ሆነው ለዘልአለም ይኖራሉ።